ፍትህ ነጻነት ህብረት

S.M.N.E

Solidarity Movement for a New Ethiopia

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

# በአትላንታው ዓለምአቀፍ ጉባዔ የንቅናቄያችን ተሳትፎ

ከአንድ ሳምንት በፊት የንቅናቄያችን መሪ አቶ ኦባንግ ሜቶ የLeon H. Sullivan Foundation ባቀረበላቸው ጥሪ መሠረት Africa Policy Forum: A Vision for the 21st Century በሚል ርዕስ በአትላንታ ጆርጂያ በተደረገው ስብሰባ ላይ መገኘት እንዲችሉ የገንዘብ ማሰባሰብ ማድረጋችን ይታወሳል፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ከተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የመጡ ስምንት ፕሬዚዳንቶች የተካፈሉ ሲሆን ታዋቂ ግለሰቦች እንዲሁም የመንግሥታት ተወካዮች ከአሜሪካ፣ አፍሪካ፣ ካሪቢያን፣ እስያ እና አውሮፓ የተገኙበት ከፍተኛ ስብሰባ ነበር፡፡ አቶ ኦባንግ በዚህ ስብሰባ ላይ መገኘት እንዲችሉ ለንቅናቄያችን አባላትና ደጋፊዎች ባቀረብነው የአጭር ጊዜ የገንዘብ ማሰባሰብ ጥያቄ ከስምንት የተለያዩ አገሮች - ኖርዌይ፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ዩክሬይን፣ ካናዳና አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሁለት ቀናት ውስጥ ብቻ ተፈላጊውን የገንዘብ መዋጮ በማድረጋቸው አቶ ኦባንግ አትላንታ በስብሰባው ላይ ለመገኘት ችለዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለእነዚህ የንቅናቄያችን ወዳጆችና ደጋፊዎች ያለንን ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ይህ ስብሰባ በ በየሁለት ዓመቱ የሚዘጋጅ ሲሆን በዚህ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ላይ በተደረገው ስብሰባ ላይ አትኩሮት የተሰጠባቸው የመወያያ ርዕሶች የሚከተሉት ነበሩ፡- ‹‹አሜሪካ በአፍሪካ ላይ ያላት ፖሊሲ››፣ ‹‹የአፍሪካን የወደፊት የኢኮኖሚ ዕድገት በውድድር፣ ንግድና ኢንቨስትመንት ማጠናከር››፣ ‹‹በአፍሪካ የንጹህ ውሃ አቅርቦት ላይ ያሉት ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸው›› ፣ ‹‹ዓለምአቀፍ የሴቶች ጉዳይ››፣ ‹‹ጣምራ ዜግነት፡ በአፍሪካውያን እና በጥቁር አሜሪካውያን መካከል ድልድይ መፍጠር›› ወዘተ ነበሩ፡፡ አቶ ኦባንግ በአፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያ እየተፈጸመ ስላለው ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለውጪ ባለሃብቶች በነጻ የመስጠት ድርጊት በተወያየው ፓናል ላይ ወቅታዊውን የኢትዮጵያ ሁኔታ በዝርዝር ከማስረጃዎች ጋር ለስብሰባው ተካፋዮች አስረድተዋል፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች አብዛኛዎቹ ላይ አቶ ኦባንግ የተሳተፉ ሲሆን የነበራቸውንም ተሳትፎ ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

## ‹‹አሜሪካ በአፍሪካ ላይ ያላት ፖሊሲ››

በዚህ ርዕስ ላይ የተደረገው ውይይት ያተኮረው ባለፉት ሁለት ዓመታት የፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደር በአፍሪካ ላይ ያለውን ፖሊሲ እና በቀጣይ ዓመታት ያሉትን አካሄዶች የዳሰሰ ነበር፡፡ ከፓናሉ አባላት መካከል በዩናይትድ ስቴትስ የአፍሪካ ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ዊሊያም ዋርድ፣ የENOUGH ፕሮጄክት መሥራች ጆን ፕሬንዴርጋስት፣ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ጸሃፊ ሱዛን ፔይጅ፣ እና ሌሎች በዚሁ ርዕስ ላይ ሰፊ ገለጻ የሰጡ ሲሆን በተለይ በአፍሪካ ከፍተኛ ግጭት የሚታይባቸውን ቦታዎች ማለትም ሶማሊያ፣ ዳርፉር፣ ደቡብ ሱዳን፣ ኮንጎ እና የአፍሪካ ቀንድ በተመለከተ ውይይት ተካሂዷል፡፡




አቶ ኦባንግ የአፍሪኮም አዛዥ ከሆኑት ጄ/ል ዋርድ  በስብሰባው ወቅት ጋር ጠንካራ ውይይት ካካሄዱ በኋላ

ከዚህም በኋላ በተካሄደው ውይይት አቶ ኦባንግ ለፓናል አባላቱ እንዲሁም ለተሰብሳቢዎቹ በኢትዮጵያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን በተለይም አሜሪካ አሸባሪነትን ለመዋጋት በሚል ሽፋን በአፍሪካ የሚገኙ አምባገነኖችን ከመደገፍ አልፈው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ማፍሰሳቸው አሜሪካ በአፍሪካ ላይ ያላትን የተሳሳተ የውጪ ፖሊሲ በጉልህ የሚያስረዳ መሆኑን ከገለጹ በኋላ በተለይ ለጄኔራል ዋርድ እና ለረዳት ጸሐፊ ፔይጅ ያቀረቡት ተግዳሮት አሜሪካ እንደ አቶ መለስ ያሉ አምባገነን በመደገፏ የሶማሊያን ውጥረት ይበልጥ ያባባሰው ከመሆን አልፎ መለስ ራሱ በዚህ ከአሜሪካ በሚያገኘው ድጋፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰብዓዊ መብቱን በመርገጥ እያሸበረ እንዳለና የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ለማያቋርጥ ቀውስ ውስጥ መዳረጉ በመናገር አሜሪካ ይህንን ተግባሯን በማቆም ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብን የመብት ጥያቄ ለማስከበር ብትጥር ዘላቂና ውጤታማ ዓላማ ማሳካት እንዴት እንደምትችል አስረድተዋል፡፡ ከዚህ ሌላ አቶ ኦባንግ ‹‹**የመለስ አገዛዝ በ2002 በተደረገው ምርጫ 99.6% አሸንፌያለሁ በማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምጽ ሲያፍን አሜሪካ ሆነች ሌሎች ለጋሽ መንግሥታት ጠንካራ ተቃውሞ ያላሰሙት ለምንድነው?**›› በማለት ጥንከር ያለ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ በመቀጠልም ኢትዮጵያውያን ለለውጥ የተዘጋጁ እና ይህንንም በተግባር ለመተርጎም ከአምስት ዓመት በፊት በተደረገው ምርጫ የሚፈልጉት መምረጣቸው ቢያሳውቁም የመለስ ፓርቲ ምርጫውን ከመስረቅ አልፎ ይህንን ድርጊት በሰላማዊ ሰልፍ የተቃወሙትን ወደ200 የሚጠጉ ንጹሃን መግደሉ በማስረጃ የተረጋገጠ ሐቅ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመጨረሻም አሜሪካ ከአፍሪካ በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ዘላቂ ግንኙነት ለመፍጠር የምታስብ ከሆነ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታትን እንዲሁም ሕዝብን መሠረት ያደረጉ የዴሞክራሲ ኃይሎችን እና ፓርቲዎችን መደገፍ ዓይነተኛ ለውጥ የሚያመጣላት እንደሆነ በአጽንዖት ገልጸዋል፡፡ ይህ የአቶ ኦባንግ አስተያየት ከፓናል አባላቱም ሆነ ከተሰብሳቢዎቹ ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘ ሲሆን ለተግባራዊነቱ ንቅናቄያችን ክትትል እንደሚያደርግ በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

## ‹‹ዓለምአቀፍ የሴቶች ጉዳይ››

በዓለምአቀፍ ሴቶች ጉዳይ ላይ ውይይቱን የመሩትና ያወያየዩት የ Mission of the Diaspora African Forum ዋና ኃላፊ ዶ/ር ኤሪካ ቤኔት፣ የቀድሞ የ Hewlett-Packard ምክትል ፕሬዚዳንት ዳያና ቤል፣ የ The Africa Society ፕሬዚዳንት ዴርናዴት ፓየሎ፣ የ Bennett College for Women ፕሬዚዳንት እና ታዋቂ የምጣኔ ኃብት ምሁር ዶ/ር ጁሊያን ማልቮ እንዲሁም የ Leon H. Sullivan Foundation ፕሬዚዳንትና ዋና ሥራአስኪያጅ ሆፐ ሱሊቫን ማስተርስ ነበሩ፡፡
የምሁራን ሴቶቹ ዘገባ ከቀረበ በኋላ በተካሄደው ውይይት አቶ ኦባንግ መድረኩን በመጠቀም ለፓናል ተወያዮቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ባላት የፖለቲካ አመለካከት ብቻ እድሜ ይፍታሽ ተብላ እስርቤት ስለምትገኝ የፖለቲካ እስረኛ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ያውቋት እንደሆነ በጉባዔው ፊት የጠየቋቸው ሲሆን የፓናል ተወያዮች ምሁራኖችም ምንም የሚያውቁት እንደሌለና አቶ ኦባንግ በዚህ ላይ ያላቸውን ለፓናሊስቶቹ እንዲሁም ለጉባዔተኛው እንዲያስረዱ በጠየቁዋቸው መሠረት አቶ ኦባንግ ስለወ/ት ብርቱካን ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡



አቶ ኦባንግ ስለ ወ/ት ብርቱካን ለተሰብሳቢዎቹ ባስረዱበት ወቅት

በመቀጠልም በአሜሪካ የሰብዓዊ መብት እንቅስቃሴ ይካሄድ በነበረበት ወቅት በትግሉ ቀዳሚ ስፍራ ከነበራት ሮዛ ፓርክስ ጋር ወ/ት ብርቱካን በድፍረቷና ለፍትሕ መቆሟ የሚያመሳስላት እንደሆነ በመጥቀስ በተለይ ጥቁር አሜሪካዉያን ሴቶች ከወ/ት ብርቱካን ጎን በመቆም እርሷ የቆመችለትን ዓላማ መደገፍ እንደሚገባቸው በአጽንዖት አሳስበዋል፡፡ በዚህም ወቅት አቶ ኦባንግ ያገኙት ምላሽ ከፍተኛ ሲሆን በተለይም ከፓናሊስቶቹ ከፍተኛ ባለሥልጣናት መካከል የተወሰኑት ይህንን የወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ አቶ ኦባንግ በየቦታው በተለይም በኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች እየተገኙ ለሴቶች እንዲሁም ለወጣቶች ግንዛቤ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርበውላቸዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተወካይ ዋሂድ በላይ[1] አቶ ኦባንግን መቃወም

አቶ ኦባንግ በስብሰባው በክብር የተጠሩ እንደመሆናቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በኢትዮጵያ ስላለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የፖለቲካ ምህዳር መዘጋት፣ ሙስና፣ የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ፣ የፕሬስ ነጻነት መነፈግ፣ ወዘተ ተሰብሳቢዎቹ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደረጉ ሲሆን ይህን በኢትዮጵያ ያለውን ጭቆና በማጋለጣቸው የተቆጩ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ተወካይ በስብሰባው ላይ

[1] http://www.ethiopianembassy.org/AboutEmbassy/AboutEmbassy.php?Page=EmbassyStaffs.htm

ተቃውሞውን ገልጾ ነበር፡፡ ይህ ግለሰብ አቶ ዋሂድ በላይ[2] የሚባል ሲሆን ግለሰቡ ከኢትዮጵያ ከመጣ ሁለት ወር እንደሆነው በመግለጽ በኤምባሲው የሕዝብ ግንኙነት ተግባር ላይ የተሰማራ በመሆኑ አገዛዙን በመወከል እና በተለይ በአሜሪካ በእንደዚህ ዓይነት ስብሰባዎች ላይ በመገኘት የተላከበትን ዓላማ ለማሳካት እንደሚንቀሳቀስ እሙን ነው፡፡ በመሆኑንም በዚህ ስብሰባ ይኸው ግለሰብ ‹‹እንደ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ያለበት አገር በአፍሪካ አይገኝም፣ ሙስና ጨርሶውኑ በኢትዮጵያ የሌለ ክስተት መሆኑን፣ የመሬት ሽያጩም ለ99 ዓመት በሊዝ የሚሰጥና መንግሥት በፈለገ ጊዜ ከቦታቸው እንደሚያስነሳቸው›› በመናገር ማስረጃ ያልተደገፈ የፈጠራ ንግግር ቢያደርግም አቶ ኦባንግ ተሰብሳቢውን በኢትዮጵያ ስላለው ተጨባጭ ሁኔታ በማስረጃ የተደገፈ ትንተና የሰጡ በመሆናቸው ግለሰቡ ያሰበውን ዓላማ ሳያሳካ ለመመለስ በቅቷል፡፡

## የ Grey's Anatomy መሪ ተዋናይ አይዛያ ዋሽንግተን የሰጠው ምላሽ

በስብሰባው ላይ ከተገኙት ታዋቂ ግለሶች መካከል Grey's Anatomy የተባለው ተከታታይ የቴሌቪዥን ፊልም መሪ ተዋናይ የሆነው አይዛያ ዋሽንግተን ነው፡፡ ስለ ጣምራ ዜግነት በተደረገው ውይይት ላይ ሲናገር ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት ዝርያውን በማስጠናት የሴራሊዮን ዝርያ ያለው መሆኑን በማረጋገጡ በቅርቡ የጣምራ ዜግነት ፓስፖርት መያዙን ገልጾ ነበር፡፡ በመቀጠልም ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በአፍሪካ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሲያደርግ እንደቆየ ሆኖም ስለኢትዮጵያ ብዙም እውቀት እንዳልነበረው ነገር ግን በቅርቡ አንድ ኢትዮጵያዊ ቀርቦ እንዳነጋገረውና በኢትዮጵያ ውስጥ የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ የሚያስችል ሥራ አብሮት እንዲሠራ ጥሪ አቅርቦለት እንደነበር ሆኖም ግን ግለሰቡ የጎጥ ፖለቲካ ከሚያራምደው አገዛዝ የተላከ መሆኑን ከጊዜ በኋላ የተረዳ መሆኑን አስታውቋል፡፡ ከዚህ በኋላ አይዛያ ዋሽንግተን የተናገረው የስብሰባውን ታዳሚዎች ያስደመመ ነበር፡፡ በስብሰባው ወቅት ከሰማቸውና ቀልቡን ከሳቡትና ልቡን ከነኩት ንግግሮች መካከል አቶ ኦባንግ ***‹‹ከዘረኝነት ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ››*** በማለት የተናገሩት እጅግ እንደመሰጠው በመግለጽ እንዲህ ብሎ ነበር፡- ***‹‹እኛ አፍሪካ አሜሪካውያን አይደለንም፣ ጥቁር (ኒግሮ) አይደለንም፣ ዳያስፖራም አይደለንም በቀላሉ ለመናገር እኛ ሁላችንም ሰብዓዊ ፍጡሮች ነን፡፡ እኔ እንደማስበው ሁላችንም በዚህ አባባል ሥር መሰባበሰብና ይህንን ‹‹ከዘረኝነት ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ›› የሚለው አባባል ዋንኛ የሥራ ቋንቋችን በማድረግ በአፍሪካ ውስጥ አብዮት ማካሄድ ይገባናል፡፡ አፍሪካውያን በሙሉ ከዘራቸው ይልቅ ሰብዓዊነትን እንዲያስቀድሙ ማነሳሳት አለብን፡፡ ማንኛችንም ከምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ከሰሜን፣ ከደቡብ ወይም ከመካከለኛው አፍሪካ የመጣን ብንሆን፤ የቆዳ ቀለማችን በጣም የጠቆረ ወይም ሻል ያለ ቢሆን፤ እስላም ወይም ክርስቲያን ብንሆን፤ አመጣጣችን ከናይጄሪያ፣ ጋና፣ ኢትዮጵያ ወይም ከየትኛው አገር ብንሆን ሁላችንም ‹ሰብዓዊ› በሚለው ቃል ውስጥ የምንካተት ነን፡፡ እስካሁን ያወራነው ይበቃናል፡፡ በእኔ በኩል ወደትውልድ ምድራችን ሊመልሰን የሚችለውን ንቅናቄ ለመቀላቀልና ለመደገፍ ዝግጁነቴን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ ኦባንግ እንዳለው ይህ ንቅናቄ አፍሪካውያንና ጥቁር አሜሪካውያንን ለማገናኘት የሚችል ድልድይ ነው፡፡ ከእንግዲህ እነሱና እኛ የሚባል ነገር የለም ሁላችንም ‹እኛ› ነን በማለት ኦባንግ እንደነገረን ሁላችንም ከዘረኝነት በፊት ሰብዓዊነትን አስቀድመን በአንድነት እንነሳ፡፡ ስለዚህም አፍሪካውያን መልካም አስተዳደርን በየአገራቸው መመስረት እንዲችሉ፣ ሰብዓዊ መብትን እንዲያከብሩ ከሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ጋር አብረን እንቁም ፤ እንርዳቸው፡፡ በእኔ በኩል እንዲህ ዓይነቱን ንቅናቄ ለመደገፍ እንዲሁም እንደ ወንድሜ ኦባንግና ሌሎች እንደርሱ ዓይነት አመለካከት ካላቸው ጋር ለመሥራት መዘጋጀቴን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ››*** በማለት በተናገረበት ጊዜ መላው ጉባዔተኛ ከመቀመጫው በመነሳት ድጋፉን ገልጾለታል፡፡ ስብሰባው በቀጠለባቸው ቀናትም አይዛያ ዋሽንግተን ስለ ንቅናቄያችን ሰፋ ያለ ማብራሪያ እንዲሁም ወደፊት

[2] Ibid.

ምን ዓይነት ዕርዳታ ሊያደርግ እንደሚችል ከአቶ ኦባንግ ጋር ለበርካታ ጊዜያት በመገናኘት ጠቃሚ መረጃዎችን ሲቀበል ቆይቷል፡፡




አይዛያ ዋሽንግተን ስሜት ቀስቃሽ የሆነውን ንግግር ባደረገበት ወቅት፡፡ በፎቶው ላይ እንደሚታየው የሴራሊዮን ተወላጅ በመሆኑ ከአገሪቱ የተሰጠውን ፓስፖርት ሲያሳይ ነው፡፡

በመጨረሻም አቶ ኦባንግ በአትላንታ ከተማ ከሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጋር በወቅቱ የአገራችን ጉዳይ፣ እንዲሁም በውጪ ያለው ኅብረተሰብ ትግሉን በምን መልኩ ማገዝ እንዳለበት ግልጽና ጠቃሚ ውይይቶችን አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያውያኑም ንቅናቄውን ለማገዝና የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለመወጣት ያላቸውን ጽኑነት ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ የአቶ ኦባንግ ጉብኝት ውጤታማና በርካታ ጉዳዮችን የዳሰሰ በመሆኑ ለንቅናቄያችንም ሆነ ለሚደረገው ትግል የሚሰጠው ድጋፍ እሙን ነው፡፡ በተለይም ከታዋቂ ግለሰቦች ጋር በመገናኘት የንቅናቄያችን ዓላማ ለማስፋፋትና በተቻለ መልኩ ዓለምአቀፋዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዳ በመሆኑ የአትላንታው ስብሰባ አመርቂ ውጤት ያስገኘ በመሆኑ ለዚህም ልባዊ ድጋፋችሁን ላደረጋችሁ በሙሉ ያለንን ከፍተኛ ምስጋና ስናቀርብላችሁ ወደፊትም በምናደርገው መጠነሰፊ እንቅስቃሴ የዘወትር ድጋፋችሁ እንዳይለየን እንጠይቃለን፡፡

ፈጣሪ አገራችንን ይጠብቅ እኛንም ለምንመኘው ሰላም፣ ፍትሕና ነጻነት ያብቃን፡፡

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

**************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ የንቅናቄያችንን ዋና ዳይሬክተር ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ማግኘት ይችላሉ፡፡*

